MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION
ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት
P. O. Box 55321, Washington, DC 20040-5321
Tel: (202)-677-0094
Web: http//www.moreshwegenie.org/

*ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት*　　*ሰኞ ጥር ፲፬ ቀን ፪ሺህ፲ዓ.ም.*　　*ቅጽ ፮ቁጥር ፬*

# በወልድያ ከተማ ነዋሪዎች ላይ የተፈጸመውን ግፍ፣ የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት በጽኑ ያወግዛል!

*እስከ መቼ ዋይታ! መከራና ለቅሶ!*

*በእኛ ላይ ይደርሳል መልሶ መላልሶ!*

«የትግራይ ተራሮች የዐማራ መቃብር ይሆናሉ» በሚል መፈክር፣ ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ዘብ የቆሙ ኢትዮጵያውያንን ከ1967 እስከ 1983 ባሉት 17 ዓመታት ውስጥ፣ የሁሉንም ነገድ ልጆች በዐማራነት ፈርጀው በግፍ መጨፍጨፋቸውን፣ በምርኮ የያዙዋቸውን ወታሮች የወባ መድኃኒት ነው ብለው፣ የውሻ መግደያ መርዝ ግተው በምድር ውስጥ በገነቧቸው እስር ቤቶች መፍጀታቸውን እናውቃለን። ሁሉም ግን የተገደሉት በዐማራነት ስም  መሆኑን ስንገነዘብ ደግሞ፣ የትግሬ ወያኔ በዐማራ ላይ ያለው ጥላቻ የቱን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል። ዛሬ ይህ መፈክር፣«የኢትዮጵያ ተራሮችና ሸለቆች፣ ከተሞችና ገጠሮች የዐማራ መቀበረያ ይሆናሉ»፣ በሚል የተቀየረ እንደሆነ፣ በአገሪቱ ውስጥ በዐማራው ነገድ ላይ የሚፈጸሙት ግድያዎችና ግፎች አፍ አውጥተው እየተናገሩ ነው። «ዐማራ ካልጠፋ የትግራይ ሕዝብ ማኅበራዊ ሰላም አያገኝም» በሚለው መመሪያቸው መሠረት ለአንድነትና ለኢትዮጵያዊነት የቆሙ የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ነገድ ልጆች በግፍ መገደላቸውን  ከትግሬ-ወያኔ በቀር የሌሎች ነገድ ልጆች አናውቅም ሊሉ የሚችሉ፣ አንድም መረጃ የሌላቸው፣ ሌላም በጥቅም የተገዙ ሆድ አደሮች ብቻ ናቸው። ይህ ካልሆነ አቶ ገብረመድኅን አርኣያ በተከታታይ በጠለምት፣ ወይቃይት፣ ተንቤን፣ ሽሬ፣ ደጀና፣ ዐድዋ  ወዘተ በሚገኙ የባዶ ስድስት የማሰቃያ ጉድጓዶች ያለቁትን ወገኖቻችንን ያለመሰልቸት በዝርዝር ነግሮናል። የእኛ ችግር የመረጃ እጦ ሳይሆን፣ ዕውነቱ ሲነገረን፣ ነግ ለእኔ ብለን አስፈላጊውን ዝግጅት አለማድረጋችን ነው።

ይህም በመሆኑ፣ የትግሬ-ወያኔ ሥልጣንን ከተቆጣጠረ በኋላ፣ ዐማራውን በገዥ መደብነት፣ በጨቋኝነት፣ በትምክህተኝነት፣ ባለፉ ሥርዓቶች አቀንቃኝነት ስሞች ፈርጀው፣ የጎጃምንና የጎንደር ክፍለ ሀገር ነዋሪ ዐማራን «ሽፍታ ምንጠራ፣ መሬት ድልድል» የሚሉ የዘመቻ ስሞችን ሰጥተው ዐማራውን ትጥቁን ማስፈታታቸውን፣ መሬቱን መቀማታቸውን የምናስታውሰው በምሬት ነው። ድርጊቱ ትክክል አይደለም ያሉትን ልበ ሙሉ ጀግኖቻችንን በገፍ መግደላቸውና ማሰራቸው እንዲሁም ማሰደዳቸውን እናስታውሳለን። የወልቃይት፣ ጠገዴ፣   ጠለምትና ሠቲት ወረዳዎችን በመሬቱ ላይ ትግሬን ለማስፈር ከ1972 ዓም ጀምሮ በተከታታይ ዐማራዎቹን በግፍ መግደላቸው፣ ማሰራቸውና እንዲሰደዱ መደረጉ የአደባባይ ምስጢር ነው። በ1985 ጎንደር አደባባይ ኢየሱስ ለፀሎት በተሰበሰቡ የከተማው ነዋይዎች ላይ የደደቢት ሠራዊት በመትረጌስ የጨፈጨፋቸው ሰዎች ደም ዛሬም እየጨኸ ነው። በ1985 ዓም የቡትሮስ ቡትሮስን የወቅቱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊን የኢትዮጵያን ጉብኝት ዓላማ በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ በወጡ ተማሪዎች ላይ የአገዛዙ አፋኝ ወታደራዊ ቡድን የገደላቸውን ተማሪዎች «በኢሠፓ» አባልነት እና በዐማራነት የወነጀላቸው እንደሆነ እናስታውሳለን።

ከ1983 እስከ 1987 በሐረርጌ፣ በአርሲ፣ በወለጋ፣ በኢሉባቡር በተለያዩ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ይኖሩ በነበሩ ዐማሮች ላይ የተፈጸመውን የዘር ማጥፋት ግፍ እነርሱ ቢረሱት፣ «የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም» እና የዐማራው እናቶች አይረሱትም። የበደኖን፣ የወተርን የአርባጉጉን፣ የመቻሬን፣ የአሰቦት ገዳምን ዕልቂት መቼም ቢሆን፣ ዐማራው ቀርቶ፣ ሰብአዊ ፍጡር ይረሳዋል ተብሎ የማይታሰብ ነው። በነዚህ ዓመታት በመሀል ኢትዮጵያ ስማቸውና አድራሻቸው የተመዘገቡ ከ500 በላይ ዐማራዎች በግፍ በወያኔ ነፍሰ በላይ ሰላዮች መገደላቸውን በወቅቱ «አንድነት» የተሰኘው የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት ልሳን «ሰቆቃው ዐማራ» በሚል አምዱ ሥር ይፋ ማድረጉን አንዘነጋውም።

በ1993 በምሥራቅ ወለጋ በሦስት ተከታታይ ጊዜ በጥቅሉ ከ50 ሺ በላይ ዐማሮች መፈናቀላቸውን፣ መገደላቸውንና ለከፍተና ስቃይና መከራ መዳረጋቸውን የዓለም ብዙኃን መገናኛ መሣሪያዎች ይፋ ማድረጋቸውን እናስታውሳለን። ከተገደሉት መካከል የ600 በላይ ዐማሮች  ማንነትን «ምጽአተ ዐማራ» የተሰኘው የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት ጥናታዊ መጽሐፍ ገጽ304 እስከ 318 ተዘርዝሯል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ይህን በወለጋ ክፍለሀገር ይኖሩ በነበሩ ዐማሮች ላይ የደረሰውን ግፍና መከራ «ጦቢያ» መጽሔት ቅጽ 8 ቁጥር 8 በ1993 የልዩ ጥንቅር አምዱ ሥር በዝርዝር አስፍሯል።

በሐረርጌ ይኖሩ በነበሩ ዐማሮች ላይ ከ1984 እስከ 1985 ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በጋራ ሙለታ፣ ወተር፣በደኖ፣ ድሬደዋ፣ሀብሩ ፣አሰቦት ገዳም ወዘተ በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ዐማሮች በዘረኛው የትግሬ-ወያኔ አገዛዝ በግፍ ተገድለዋል።

ከ2002 እስከ 2005 ባሉት ዓመታት ዐማራውን ከአባቶቹ አገር፣ ከፋ/ጅማ፣ ከጎጃም/ መተከል፣ ከወለጋ/አሶሳ ዐማራውን ከአካባቢው ለማስወጣት በተደረገው የዘር ምንጠራ ዘመቻ፣ ከ78 ሺ በላይ ዐማሮች እንዲፈናቀሉ ተደርጓል። በዚህ ማፈናቀል ሂደት አያሌ ዐማሮች ተገድለዋል። ተደብድበዋል። ለአካል ጉዳት ተዳርገዋል።

ከ2008 ዓም ላይ የወልቃይት ማንነት ጥያቄ ባስከተለው ሕዝባዊ ተቃውሞ አያሌ የጎንደር፣ የባሕርዳር፣ የዳንግላ፣ የደብረማርቆስ፣ የደባርቅ፣ የደብረታቦር፣ የወረታ፣ የጋይንት፣ የአዲስ ዘመን፣ ወዘተ ከተሞች ነዋሪ ዐማራ በገፍና በግፍ መገደሉ፣ መታሰሩን ለስቃይ መዳረጉ አይዘነጋም። ይህን ሕዝባዊ አመጽ ተከትሎ የአገዛዙ የአፈናና የእመቃ መዋቅር በመሽመድመዱ ምክንያት ለአንድ ዓመት በዘለቀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣ የጎንደር  እና የጎጃም ክፍለሀገር እንዲሁም የሰሜን የሸዋ ዐማራ በመቶ ሽዎች የሚቆጠር ሕዝብ መታሰሩን፣ አያሌዎች መገደላቸውን የብዙኃን መገናኛ መሣሪያዎች ይፋ ማድረጋቸው ይታወሳል።

ይህ ሁሉ ሲሆን፣የዐማራው ምሑር እና ወጣት፣ «የፋሲካው ሙክት፣ በገናው ይስቃል» የሚሉት የአባቶቻችን አባባል ዕውነት ሆኖ፣ ባንድነት መቆም ተስኖት፣ የተለያዩ ስበቦችን በመደርደር ወያኔ ያላንዳች ይሉኝታና ህግ ባይ ተበትኖ ያገኘውን ዐማራ እንደልቡ ባሻው መልክ መግደሉን፣ ማፈናቀሉን፣ ማሰሩን፣ ማሰደዱን ለ27 ዓመታት ቀጥሎበታል። የዐማራው አለመደራጀትና ለሚደርስበት ጥቃት መካች ልጅ አለመኖሩን የተረዳው ወያኔ፣ በሰበብ አስባቡ የሕዝብ ድምፅ ጎላ ብሎ በተሰማ ቁጥር ዐማራውን እያደነ መፍጀትን ተያይዞት እያየን ነው። የ2010 ን የጥምቀት እና የቅዱስ ሚካኤልን ዓመታው ንግሥ በዓል ለማክበር በወልድያ ወደ ጥምቀት ባሕሩ ባቀኑ የወልድያ ከተማ ነዋሪ ሕዝብና ወጣቶች ላይ የአጋዚ ሠራዊት የፈጸመው ጅምላ ግድያና ጭፍጨፋ ያለፉት ጭፍጨፋዎች ተከታይ ነው።

የትግሬ ወያኔ ዐማራው ጠላቴ ነው ብሎ ሲነሳ፣ የዐማራውም ወጣት «ትግሬ ጠላቴ ነው» ቢልና ከጥቃት ለመከላከል ዝግጁ ቢሆን፣ወልቃይት ጠገዴን፣ ጠለምትን፣ ራያና አዘቦን ወደትግራይ አካሎ ትግሬን ሲያሰፍርበት፣ የለም አይሆንም ብሎ ዐማራው በአንድነት ቢቆም፣ ባጭሩ ከላይ በየተራ በዐማራው ላይ የተፈጸሙት ግፎች ሲፈጸሙ፣ ዐማራው ለምን ብሎ በአንድነት ቢቆም ኖሮ፣ ትናንትና ዛሬ በወልደያ ከተማ የተፈጸመው ግፍ ሊፈጸም ቀርቶ ሊታሰብ አይችልም ነበር። ለዐማራው መጠቃት ዋናው ምክንያት፣ የትግሬዎቹ መደራጀትና የሥልጣን ባለቤት መሆናቸው ሳይሆን፣ ዐማራው የወያኔን ማንነትና በዐማራው ላይ የሰነቀውን ጥላቻ አለመረዳትና ማንነቱን ለማስጠበቅ ዝግጁ አለመሆኑ ነው።

ስለሆነም« ላለፈ ክረምት ቤት አይሠራም፤» ቤት የሚሠራው ለሚመጣው ክረምት ነው። ካለፉ ድርጊቶች ትምህርት ይቀሰማል እንጂ፣ ድርጊቶቹን መመለስ አይቻልም። በዐማራው ላይ የትግሬ-ወያኔ እስካሁን የፈጸማቸው ግፎች ለወደፊት ትምህርት ሰጭ በሆነ መንገድ የምንማርባቸው እንጂ፣ የምንመልሳቸው አይደሉም። በመሆኑም ድርጊቶቹን ማወቅና ለትውልድ ከማስተላለፍ በተጓዳኝ፣ የዐማራው የአሁኑ ትውልድ ቀዳሚ ሚናው አድርጎ ሊሠራበት የሚገባው፣ ያለፉት ዓይነቶች ዘርን መነሻና መድረሻ ያደረጉ ጥቃቶች እንዳይደገሙ ራሱን ለመከላከልና ማንነቱን ለማስቀጠል በማንነቱ ዙሪያ መደራጀት ለይደር የማይባል መሆኑን ማወቅና አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ምክንያት የለሽ ሆኖ መቆም ነው። እየተጠቃን ያለነው በዘር ነው። የምንድነውም ራሳችን በማንነታችን ስንደራጅና ስንመክት ብቻ ነው። «ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይደርስም።» ጩኸታችን ሰሚ አገኝቶ አጋር የሚኖረን በቅድሚያ እኛ የጉዳዩ ባለቤቶች በአንድነት ድምፃችንም ሆነ ተግባራችን ጎልቶ መውጣትና መታየት ሲችል ነው።

ዛሬ በቁጭት የምናያቸው በወልደያ እህት ወንድሞቻችን ላይ የተፈጸመው ግፍ፣ ትናንት ጎንደር፣ ባሕርዳር፣ ደብረብርሃን ወዘተ የተፈጸመ ነው። በዘመነ ወያኔ አገዛዝ ለዐማራው መገደልና መፈናቀል እንግዳ አይደለም። እንደባህል እና መልካም ሥራ ሆነ የዘለቀ ነው። ለዚህ ዓይነቱ ድርጊት በተከታታይነት መቀጠል ደግሞ የራሱ የዐማራው ለምን ብሎ ራሱን ከጥቃት ለመከላከል ዝግጁ አለመሆኑ እንደሆነ ብግልጽ ይታያል። ስለሆነም፣ ከእንግዲህ፣ የወልድያ ወገኖቻችን ዕልቂት፣የመጨረሻ እንዲሆን ለማድረግ፣ ዐማራው ግዳይ የሚጥልበት፣ ጠላቱን የሚያንበረክክበት እንጂ፣ መርዶ ነጋሪ፣ አልቃሽና አስለቃሽ የሚሆንበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። ግፉ ሊገታ ይገባል። ይህ የሚሆነው ደግሞ፣ የዐማራው ወጣት፣ ልክ እንደወያኔዎቹ ሁሉ፣ በቃን ብሎ ወያኔን መግደል ሲጀምር ብቻ ነው።

ከምስለ-ገጽ አርበኝነት ወደ ነፍጥ አንጋች አርበኝነት ትግሉን ማሸጋገር ስንጀምር፣ ወያኔ ያኔ፣ ከዚያም ቤት እሳት አለ ብሎ ደጋግሞ እንዲያስብና ወደ ጎሊናው እንዲመለስ ማድረግ ለነገ ቀጠሮ የምንይዝበት ጉዳይ መሆን የለበትም። ለዚህም እንዲረዳ ዛሬ አነሰም አደገ ለዐማራ ድምፅ እየሆኑ ያሉ ድርጅቶች በማቆጥቆጥ ላይ እንዳሉ እየተሰማ ነው። ወጣቱ የዐማራ ልጅ፣ የነዚህን የዐማራ ድርጅቶች ፕሮግራሞች በማንበብ የተሻለ ነው የሚለውንና ያመነበትን ድርጅት በመቀላቀል ለትግሉ ገፈ ኃይል መሆን ይጠበቅበታል። ስንደራጅ፣ ኃይል እንሆናለን። ስደራጅ እንጠነክርለን። ስንደራጅ፣ የማድረግ ብቃታችን ይጎለብታል። ስንደራጅ አሸናፊዎች እንሆናለን።

ስለሆነም በወልድያ ከተማ የፈሰሰውን የወገኖቻችን ደም የምንመልሰው፣ ተደራጅተን ለዳግም ጥቃት እንዳንጋለጥ ሁለንተናዊ አቅማችን በታቀደና በተጠና መንደግ ኃይላችን በወያኔ እንቅስቃሴ ላይ ማሳረፍ ስንችል ነውና፣ ኑ እንደራጅ! እያሉ የዐማራው የሲቪክና የፖለቲካ ድርጅት የሆኑት ፤የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት እና የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ጥሪያቸውን በተጎዱ ዐማራ ወገኖቻችን ስም ያቀርባሉ።

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ዐማራን ከፈጽሞ ጥፋት እንታደጋለን!

ዐማራነት በኢትዮጵያዊነት ያብባል!